**የጥላሁን ገሰሰን ሞት መግታት ይቻል ነበር!**

**ከዚህ በታች ያለው ጽሁፍ ጋዜጠኞች ከጥላሁን ገሰሰ ባለቤት ወይዘሮ ሮማን በዙ ጋር ካደረጉት ቃለምልልስ ላይ የተወሰደ ነው:: ከጥላሁን ባለቤት ቃል እንደምንረዳው: የጥላሁን ሞት ያለምንም ጥርጥር መግታት ይቻል ነበር - ተገቢዉን አስቸኳይ የህክምና እርዳታ በተገቢው ጊዜ በተገቢው ባልሙያ ቢአገኝ ኖሮ:: ለጥላሁን ሞት ትብብር ካደረጉት: ተገቢ ሆስፒታል/ክሊኒክ/የህክምና ባለሙያ እጥረት እንዲሁም ብልሹ የመኪና መንገድ መሆናቸውን ከቃለ ምልልሱ እንረዳለን::**

*"..ለራሴም አስደንጋጭ ነው የሆነብኝ የጥላሁን:: በሰላመ ነው የመጣነው:: አመት ከሶስት ወር አሜሪካን አገር ስንቀመጥ አንድ ቀን ሆስፒታል ተኝቶ አያቅም:: በደንብ ህክምናው እየተደረገ ምን እያለ ደግሞ እስቲ..ብዙ አሜሪካን አገር መቀመጥ አይወድም ጥላሁን..ፋሲካም ነው..ፋሲካን አስታከን ደግሞ ሌላ ስራ..ሲዲ ሊሰራ የጀመረው አለ..እሱን ለመስራትና በዛዉም እረፍት አራጋለሁ ብሎ ነው የመጣው::*

*መጣን አውሮፕላን ውስጥ መቀመጥ አይበልው..ህዝቡ በደስታ..እንዴት አምሮበታል(ጥላሁንን)..ሰው ለመሞት ካማረ ጥላሁን አንድ ምሳሌ ነው ማለት ነው:: መተኛት አልቻልንም አውሮፕላን ዉስጥ:: መጣን..ገባን..ለሰውም እንዲቀበለን ፋሲካ ነው አትንገሪ አለ..ለአንድም ሰው አልነገርንም ከቤተሰብ በስተቀረ።*

*ፋሲካም ተበላ..ተጠጣ...ቡናም ተፈላ..ሲመሻሽ ቢቃ እንተኛ ተባባልን..እሱ ወጣና ተኛ..እኔ ትንሽ እንቅልፌ እስኪመጣ ከነሱ ጋር ሌላ መኝታ ክፍል አለ እዛ ቁጭ ብዬ አወራለሁ..አንቺ እንቅልፍሽ አልመጣም አትተኚም ይለኛል..መጣሁ እንቅልፌም እስኪመጣ ድረስ እላለሁ..አውሮፕላን ዉስጥ ትንሽ ተኝቼአለሁ እለዋለሁ..እሱን ሁሉ በሆዴ ነው አንዳንዴ..ኧረ ልቤ ልክ አይደለም ይለኛል..እንዴ ያቺን መድሃኒት አልወሰድክም እንዴ ብዬ ሄድኩና አንድ መድሃኒት ወሰደ..ቢቃ ትንሽ ተረጋጋ..የምንጫወተውን ወሬ ሁሉ እየነገርኩት አስቀዋለሁ..አሁን ቢቃ እነሱም ጨዋታችን አለቀ እንቅልፋችንም መጣ።*

*እኔም ገብቼ ገና መብራትም አላጠፋሁ ገና ጋደም ልል ስል..ቆይ ቆይ መብራቱን አታጥፊ ይሄ ነገር ትንፋሼ ልክ አይደለም አለና ተነስቶ ቁጭ አለ..እንዴ ዛሬ ደግሞ ምንድነው ለየት ያለ ነገር አልኩና ከጅርባው ነካ ነካ ሳደርገው..ይሄ አስም እንደያዘው ሰው ሆነብኝ..ላቡም እንዲሁ ይንቆረቆራል..ሉሉ አልኩና ተነሱልኝ አልኩና እነሱን ቤተሰብ ጠርቼ አፋፍሰን መኪና እንዴት እንደነዳሁ አለውቅም እዚህ ቤተ ዛታ ሄድን*

*..እዛም ስንሄድ አስም አለው አሉኝ..ኧረ አስም የለዉም የልብ ኬዝ አለዉ ግን አስም የለዉም..ባካችሁ ኦክስጅን እንኳን ባይሆን ስጡት ትንሽ የሚተነፍስበት..እሱም ዶክተር ትንሽ የምተነፍስበት እባካችሁ እያለ..የለም የለም የልብ ህሙማን ህክምና ዶክተር ኢንተርናሽናል የሚባል አለ እዛ ሂዱ አሉን..የቱ ጋር ነው ስንል..ጎተራ ጋር ተባልን..*

*በወሎ ሰፈር አርገን በጎተራ ጋር ስንሄድ..ደግሞ መንገዱ እኔ ከአመት በላይ አላየሁትም ውልቅልቁ ውቱአል..እነዚህ ኧረ ቀስ እያልሽ ንጂ ገደል ልንገባ ነው ሲሉኝ..በዛ ሰአት የሚተነፍሰው ሁሉ እየቀነሰብኝ መጣ..መጨረሻ ላይ ይሄ የልብ የተባልነውም ቦታ ጠፋን..የት ነው ሌላ ቅርብ ክሊኒክ የምናገኘው ስንል...ሰናይ ክሊኒክ ተባለ..ሰናይ ክሊኒክ ገባን..ዶክተር በስንት ምክንያት ያው ተንኳክቶ ተጠራ..እባክህ ጥላሁን ገሰሰ ነው ሉሉ እላለሁ ሜዳዉን ይዤ ድረስለት እባክህን እባክህን ኦክስጅንም ቢሆን ሌላ ህክምና ቦታ እስኪደርስ ነፍሱን እባክህ እባክህ አድርስልኝ አልኩኝ..እሱግን ኦሬዲ እየቀዘቀዘ መቷል እየቀነሰ መቷል..ከዛ በህዋላማ ቢቃ ምኑን ነው የምነግርሽ.."*

**በጤና አቅርቦት ጉድለት ህይወቱ የሚያልፈዉን ኢትዮጵያዊ ቤቱ ይቁጠረው እያልኩ መንግስት ላወጣው የህዘን መግለጫ አድናቆት ቢሰማኝም: ለአስራ ስምንት አመት ስልጣንን በማናለብኝነት ተቆናጦ የጤናን እንዲሁም ሌሎች መሰረታዊ አቅርቦቶችን ለህብረተሰቡ በመንፈግ በግልጽ ከሚታዩት በደሎች በተጨማሪ ህብረተሰቡ እየተጎዳ እንደሆነ ይኸው ከላይ የተመለከትነው ነው።**

**እግዚአብሄር የጥላሁን ገሰሰን ነፍስ ይማር!**

**ነጻነት የጥላሁንን ፈለግ እየተከተለ ላለው ለቴዲ አፍሮ!**

**ፍቅር እና ሰላም ለ ኢትዮጵያችን!!**

isoloda@gmail.com – April 20, 2009